MORESH WEGENIE AMARA ORGANIZATION
ሞረሽ ወገኔ የዐማራ ድርጅት

8221 Georgia Avenue, Silver Spring, MD. 20910

- email: hq-office@moreshwegenie.org
- website: www.moreshwegenie.org

*ሞረሽ ወገኔ የዐማራ ድርጅት* *ሕዳር ፲፯ ቀን ፪ሺህ፲፩ዓ.ም.* *ልዩ ዕትም ፩/፲፩*

# የሞረሽ ወገኔ ዐማራ ድርጅት የማዕከላዊ ምክርቤት 10ኛ መደበኛ ስብሰባ

## የአቋም መግለጫ!

እኛ የሞረሽ ወገኔ የዐማራ ድርጅት (ሞወዐድ) ማዕከላዊ ምክር ቤት አባሎች፣ በድርጅቱ መተዳደሪያ ደንብ መሠረት የማዕከላዊ ምክር ቤቱን 10ኛ መደበኛ ስብሰባ ቅዳሜ ሕዳር 15 ቀን 2011 ዓ.ም. (Saturday November 24, 2018, ) አድርገናል። ባደረግነው ሠፊ ውይይት ፣በቀረበው የሞወዐድ ሥራ አስፈጻሚ ሪፖርት ላይ የሚስተካከሉትን እንዲስተካከሉ፣ የሚጨመሩትን እንዲጨመሩ ሀሳብ በማቅረብ ሪፖርቱ የድርጅቱ ቋሚ ሰነድ ሆኖ እንዲያዝ ጸድቋል፡፡ በጉባኤአችን ወቅት በቀረበው የሥራ አስፈጻሚ ሪፖርትና የቁጥጥርና ፍተሻ ኮሚቴ ማሳሳቢያ ሰነድ መነሻነት ድርጅቱ የቆመለትን ዓላማ በማሳካት ረገድ አካላትና አባላት ምን ማድረግ እንደሚጠበቅባቸው በስፋት ተወያይተን በሚከተሉት ጉዳዮች ላይ የአቋም መግለጫ አውጥተናል።

1. ሞረሽ ወገኔ የዐማራ ድርጅት፣ የዐማራን ነገድ ከፈጽሞ ጥፋት የመታደግና ድምፅ አልባ ለሆነው ዐማራ ድምፅ ለመሆን ለቆመለት ዓላማ ስኬት ዕውን መሆን፣ የዐማራው ድምፅ ከአጽናፍ እስከ አጽናፍ እንዲያስተጋባ፣ የዓለም ማኅበረሰብ በዝምታ፣ የነገዱ ምሁራን ደግሞ በቸልታ የሚመለከቱት የዘር ጥፋትና የዘር ጽዳት ወንጀል እንዲቆም፣ ወንጀለኞች ለፍትሕ እንዲቀርቡ እገዛና ድምፅ የሚሆን «ዐማራ ድምጽ ራዲዮ[ ዐድራ ]» የተሰኘ የራዲዮ ጣቢያ ላለፉት ሁለት ዓመታት ሳይቋረጥ አገልግሎት በመስጠት ላይ ይገኛል። ይህ የራዲዮ ጣቢያ በቅርቡ በተፈጠረው አንጻራዊ በር ወደ አገር ቤት ገብቶ ለኢትዮጵያ ሕዝብ ተጨማሪ አማራጭ የመረጃ ምንጭ ከመሆን ባሻገር፣ ድምፁ ለታፈነው የዐማራው ነገድ ልሣን እና አንደበት በመሆን፣ ሕዝብን ለማንቂያ፣ ለማስተማሪያ፣ ለማሳወቂያና ለማደራጃነት ጉልህ ሚና ሊጫዎት እንደሚችል ምክር ቤቱ አምኖበታል። ሞረሽ ወገኔ ዐማራ ድርጅት-ለዐማራ ድምጽ ራዲዮና ቴሌቪዥን ፕሮጀክት ገንዘብ ለማሰባሰብ እንዲያስችለው፣ በተለያዩ ከተሞች ሕዝባዊ ስብሰባዎችን ማካሄድ ወሣኝ መሆኑን ሙሉ ስምምነት ላይ ደርሰናል ፡፡ በዚህ ረገድ እስካሁን የራዲዮኑን ፕሮግራም ሥራውን ለማስመቀጠል የተደረጉት ጥረቶች ተጠናክረው እንዲቀጥሉ ተስማምተናል፡፡ የዐድራ ቦርድ እንደ አቅማችን በተጨባጭ እውነቶች ላይ ቆሞ የሞረሽ ወገኔ ዐማራ ድርጅት ሥራ አስፈጻሚ ኮሚቴ በሚስጠው መመሪያ መሰረት ተጠናክሮ መቀጠል እንደሚያስፈልግ ተመክሮበታል፡፡ ለራዲዮው መርሐ-ግብር ወደ ላቀ ደረጃ ማደግ ወሣኝ የሆነው ገንዘብ በማያቋርጥ መልኩ ለማሰባሰብ ፣ ልዩ ልዩ የገቢ ምንጮችን በመጠቀም የገንዘብ አቅሙን ለማጎልበት አካላትና አባላት የምንችለውን ሁሉ ለማድረግ በድጋሚ ቃል ገብተናል። ከሁሉም በላይ ገቢው አስተማማኝ የሚሆነው የራዲዮኑ ደጋፊዎች በቋሚ አባልነት የቻሉትን ያህል በየወሩ መክፈል ሲችሉ ስለሆነ፣ በዚህ ረገድ ከራሳችን ጀምረን በየአካባቢያችን የሚኖረውን ዐማራ የሆነውን ብቻ ሳይሆን፣ ሰብአዊነት የሚሰማቸውን ሰዎች ሁሉ ስለ«የዐማራ ድምጽ ራዲዮ» ዓላማ በማሳወቅ የገቢ ምንጩ አስተማማኝ እንዲሆን የየበኩላችን ሳንታክትና ሳንሰለች በትጋት ለመሥራት ዝግጁነታችን በድጋሚ አረጋግጠናል።

2. እንደዚሁም ቀደም ሲል ጠቅላላ ጉባኤ ባስተላለፈው ወሳኔ መሰረት የዐማራ ሚዲያ አገልግሎቱ እንደ “ ዐማራ ሚዲያ ማዕከል” ቁመናው የቴሌቪዥን አገልግሎት እንዲጀመር የዐማራ ሚዲያ ማዕከል ፣ ተጠናክሮ እንዲቀጥል ከማድረግ በተጓዳኝ፣ ወደ ቴሌቪዥን ለማሸጋገር በሞረሽ ወገኔ ዐማራ ድርጅት ጠቅላላ ጉባኤ ውሳኔ መሰረት የተያዘው ዕቅድ ተግባራዊ እንዲሆን የዐማራ ድምፅ ራዲዮ ድጋፍ ኮሚቴዎችን በማጠናከር የማያቋርጥ የገቢ ምንጭ በመፍጠር፤

ዐማራውን የማደራጀት፣ የማንቃትና የማሳወቅ ተግባር በተከታታይ እንዲሠራ የገንዘብ፣የዕውቀት፣ የመረጃና የሰው ኃይል ለማቅረብ ቃላችንን እናድሳለን፡፡

3. አንድ ሕዝብ ታሪኩን፣ ባህሉን፣ ቅርሱ፣ኃይማኖቱንና ማንነቱን አስጠብቆ ለተከታታይ ትውልድ ማሸጋገር የሚችለው፣ የእርሱ ተቃራኒ ከሆኑ የጥፋት ኃይሎች ራሱን መጠበቅና መከላከል ሲችል እንደሆነ ይታመናል። ለዚህም ዋናው ሥራ ትውልዱ አኩሪ ታሪኩን፤ ባህሉን፣ ቋንቋውን፣ ኃይማኖቱን፣ ፣ ዕሴቶቹን፣ በአጠቃላይ ማንነቱን በቅጡ እንዲያውቅ ሲደረግ ነው። ትውልዱ ወዳጅና ጠላቱን የሚለይበት፣ ከተለዋዋጭ ሁኔታዎች ጋር የተጣጣመ የታሪክ ግንዛቤ በተከታታይ እንዲቋጥር መሠረታዊ ዕውቀት ሊጨብጥ ይገባዋል። በተለይም ፀረ-ኢትዮጵያና ፀረ-ዐማራ የሆኑ ቡድኖችና ግለሰቦች ዐማራውን ታሪኩንና ማንነቱን ጥላሸት ከመቀባት አልፈው፣ የዘር ማጥፋትና የዘር ማጽዳት ወንጀል እየተፈሸመበት የሚገኝ መሆኑን ዓለም ያወቀው ገሃድ ሃቅ ነው።

4. በዛሬው ዘመን ግን የዐማራው ነገድ ትውልድ ዕውነታውን ባለማወቁ በአባቶቹ ማንነትና ታሪክ ከማፈር ወጥቶ፣ እንዲሸማቀቅና ከማንነቱ የመራቅ አዝማሚያ እንዲያሳይ የጣለብትን መረብ በመበጣጠስ ላይ እንዳለ እየተስተዋለ ነው። ይህን በሚመለከት የሞረሽ ወገኔ የዐማራ ድርጅት አጥብቆ ከተዋጋቸው ጉዳዮች አንዱና ዋናው በመሆኑ፣ የዐማራው ወጣት ትውልድ በአባቶቹ ማንነትና ታሪክ የሚመካና የሚኮራ እንዲሆን፣ ይህንም አስጠብቆ ለትውልድ እንዲያሸጋግር፣ የዐማራውን ማንነት፣ ታሪክና ለኢትዮጵያውነት የከፈለውን መስዋዕትነት የሚያሳይ፣ ከ1500ዓ/ም እስከ 2008 ዓ/ም ባሉት የ508 ዓመታት ታሪክ ውስጥ፣ ዐማራው የተጫወተውን አኩሪ ሚና እና «ጠላታችን ነው» ብለው በፈረጁት ኃይሎች የተፈጸመበትንና የሚፈጸምበትን የዘር ጥቃት ስፋትና ጥልቀት የሚያሳይ፣ የ «ምጽአተ ዐማራ፤ ተገድሎና ተገዳድሎ የማያልቅ፣ ተነቅሎ የማይደርቅ» የመጀመሪያ እትም አዘጋጅቶና አሳትሞ አስራጭቷል፡ ፡ አሁን ደግሞ ሁለተኛው እትም ተሻሽሎ ና ተዘጋጅቶ ሲጠናቀቅ ኢትዮጵያ ወስጥ በማሳተም ለገበያ ይቀርባል። በመሆኑም የሞረሽ ወገኔ አካላትና አባላት በእጅ ያለውን የመጀመሪያ እትምም ሆነ በቅርቡ ተጠናቆ የሚወጣውን ሁለተኛ እትም መጽሐፍ ለዐማራው ነገድ አባሎች በማሰራጨት፣ ዐማራው በመረጃ የታገዘ የተጠናከረ ትግሉን እንዲያፋፍም የምንችለውን ሁሉ ለማድረግ ዝግጁነታችን እናረጋግጣለን።

5. ምክር ቤቱ ዐማራውና ኢትዮጵያ የገጠሟቸውን ችግሮች፣ በአንክሮ መርምሯል። በመሆኑም ዐማራውም መስቀለኛ መንገድ ላይ ሆኖ ፊት ለፊቱ አፍጦ የሚያዩውን ፍጅትና እልቂት መላ ለማለት ትውልዳዊ የቤት ስራውን ለማጠናቀቅ በእልህ አስጨራሽ ትግል ውስጥ መጠመዱንም ተገንዝቧል ። ይህን ታሪካዊ የሕልውናና የዐማራ ማንነት ጥያቄ ንቅናቄ ሞረሽ ወገኔ የዐማራ ድርጅት በበኩሉ ማከናወን ያለበትን ዐማራውን የማደራጀትና የማንቃት ሥራ በአገር ቤትና በውጭ አጠናክሮ ከመቀጠል ባሻገር፣ በኢትዮጵያ አንድነት፣ ሉዓላዊነት፣ በግለሰብ ነፃነትና በሕግ የበላይነት ከሚያምኑ ድርጅቶች፣ ቡድኖች እና ግለሰቦች ጋር በመመካከር፣ ኢትዮጵያ የተጋረጡባትን እንደ አገር የመቀጠል ያለመቻል የመበታተን አደጋ ገፎ፣ ወደ ነባሩ የአባቶቻችን የአብሮነትና የመቻቻል ግንኙነት እንድንመለስ የሚያደርጉ ፖለቲካዊ፣ ማኅበራዊና መሰል ሥራዎች በልዩ ትኩረት እንዲሠሩ አጽንዖት ሰጥቶ ተወያይቷል። ለዚህ ተግባራዊነትም የሞረሽ ወገኔ ዐማራ ድርጅት አካላትና አባላት በሚኖሩባቸው አካባቢዎች፣ ባሉባቸው ባህላዊና ማኅበራዊ ስብስቦች ውስጥ የአሰባሳቢነት፣ የመልካም ዐማራዊ ኢትዮጵያዊነት ምሳሌዎች በመሆን፣ የአብሮነቱን ስሜት እንዲጎለብት የሚችሉትን ሁሉ እንዲያደርጉ ጉባዔው አሳስቧል።ሞረሽ ወገኔ የዐማራ ድርጅት የተመሠረተበትን መሠረታዊ ዓላማዎች በማስቀጠል ባለፉት ወራት ደረጃ በደረጃ ተግባራዊ ለማድረግ ያደረገውን ጥረትና የተገኘውን ውጤት በሪፖርቱ በሚገባ ከመረዳታችንም በላይ፣ ሞረሽ ወገኔ የዐማራ ድርጅት፣ የዐማራው ድምፅ ከመሆን አልፎ፣ ዐማራው በኢትዮጵያ ምድር የሚመጥነውን ፖለቲካዊ፣ ማኅበራዊ፣ ኢኮኖሚያዊ እና ሃይማኖታዊ ቦታውን ማስጠበቅና ለኢትዮጵያ አንድነት ተጠብቆ መዝለቅ የሚታገሉት ፣የዐማራ ፖለቲካ ድርጅቶች ወጥ በሆነው የመላው ዐማራ ሕዝብ ትግል ዓላማ ና ራይ ስር ተጠብቀው በአላማ አንድነት በመደጋገፍና በመሸፋፈን ታግለው እንዲያታግሉም የሞረሽ ወገኔ ዐማራ ድርጅት አካላትና አባላት ማናቸውንም ድጋፍ ለመስጠት ቃል ገብተናል።

6. የዐማራው ኅልውናም ሆነ የኢትዮጵያ አንድነት በአስተማማኝ ሁኔታ ሊጠበቅ የሚችለው የአገር ውስጥ ያለው የሕዝባዊ ተቃውሞ እንቅስቃሴ ወጥ አደረጃጀትና አመለካከት ይዞ በተደራጀ መንገድ ሲመራ ስለሆነ፣ ይህ የተቀናጀ ሕዝባዊ የህግ በላይነትና የአማራ ማንነት ጥያቄ ትግል ተጠናክሮ እንዲቀጥል ሞረሽ ወገኔ የዐማራ ድርጅት ፀረ- ወያኔ ትግል የፈጠራቸው የዐማራ ድርጅቶች በአንድ ወጥ ማዕከል ታግለው የሚያታግሉበትን ኃይል እንዲፈጠር እስካሁን ያደርግ የነበረውን ተግባሩን አጠናክሮ እንዲቀጥል ላማብቃት ቃል ገብተናል፡፡

7. ሞረሽ ወገኔ የዐማራ ድርጅት ባለፉት ዓመታት ያስጠናው «የፍትሕ አፈላላጊ ፕሮጀክት» ቀጣይ ሥራዎች ተጠናክረው እንዲቀጥሉ ፣ የዓለም አቀፍ ሰባዊ ድርጅቶች እና አግባብ ያላቸው ተቋሞች እንዲተባበሩን በማድረግ በዐማራ ወገናችን ላይ የዘር ማጥፋትና የዘር ማጽዳት ወንጀል የፈጸሙ ቡድኖችና ግለሰቦች ለፍትሕ እንዲቀርቡ የማድረጉን ሥራ በተቀላጠፈ መንገድ ለማከናወን የምንችለውን ሁሉ ለማድረግ ያልተቆጠበ ጥረታችን ተጠናክሮ እንዲቀጥል እናደርጋለን፡፡

8. ሞረሽ ወገኔ የዐማራ ድርጅት የቆመለትን የዐማራን ነገድ ኅልውና አስጠብቆ፣ የኢትዮጵያን ትንሣዔ ለማብሰር ለሚያደርገው ውስብስብ ትግል፥ የጊዜ፣ የዕውቀት፣ የመረጃ እና የሰው ኃይል በበቂ መጠን መገኘትን ይጠይቃል። የእነዚህ ሁሉ ብቸኛው ምንጭ ደግሞ ሰው ነው። ሰው ካለ ገንዘብ፣ ዕውቀት፣ መረጃ፣ ጊዜ አለ። ስለሆነም እያንዳንዱ የሞረሽ ወገኔ ዐማራ ድርጅት አካልና አባል፣ በሚኖርበት እና በሚሠራበት አካባቢ የሚኖሩ ዐማሮችን ማንነት እያጠና ሞረሽ ወገኔን እንዲቀላቀሉ የማድረግ የምልመላና የማደራጀት ሥራ ከሁሉም ሥራዎቻች ቅድሚያ በመስጠት ሞረሽ ወገኔን በሰው ኃይል ለማጠናከር ያለንን ሁለንንተናዊ አቅም በሥራ ላይ ለማዋል ቃል ገብተናል፡፡

9. ለሁሉም አቋሞቻችን መሠረቱ የአባላት በዓይነትና በመጠን መጠናከር ስለሆነ፣ በምንኖርበት አካባቢ የሚኖሩ ዐማራሮችንና የዐማራ ወዳጆችን በመለየት ትግሉን እንዲቀላቀሉ የማድረጉን ሥራ በጽናትና በቆራጥነት ወደፊት ለመግፋት ቃላችንን እናድሰናል፡፡

ዐማራን ከፈጽሞ ጥፋት እንታደጋለን!

ፈለገ አሥራት የትውልዳችን ቃልኪዳን ነው!

ሞረሽ ወገኔ ዐማራ ድርጅት

ቅዳሜ ሕዳር 15 ቀን 2011 ዓም (Saturday November 24, 2018)